www.abyssinialaw.com



9ኛ ዓመት ቁጥር 25
9th Year N° 25

ባህር ዳር ሰኔ 28 ቀን 1996 ዓ.ም
Bahir Dar July 5, 2004

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

# ዝክረ-ሕግ
# ZIKRE HIG

## OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA



| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር 10.15 Price | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | ፖ.ሣ.ቁ 312 B.O.BOX |



| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| ደንብ ቁጥር 17/1996 | REGULATION No. 17/2004 |
| በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የከተሞች አደረጃጀት ፈረጅ መወሰኛና ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | The Amhara National Regional State Cities' Organizational Category Determination and Establishment, Council of the Regional Government Regulation. |

### ደንብ ቁጥር 17/1996 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የከተሞችን አደረጃጀት ፈርጅ ለመወሰንና ለማቋቋም የወጣ የክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ

የብሔራዊ ክልሉን ከተሞች ግልፅና ተገቢ የሆኑ መመዘኛዎች አውጥቶ በፈርጆችና በንዑሳን ፈርጆች ማደራጀት ሚናቸውን ከወዲሁ ለይተው ለክልሉ

### Regulation No. 17/1996

A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE ORGANIZATIONAL CATEGORY DETERMINATION AND ESTABLISHMENT OF CITIES IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE

Whereas, It is believed that organizing cities of the National Region into categories and sub-categories on the basis of clear and appropriate criteria would

www.abyssinialaw.com



ሁለንተናዊ ልማትና ዕድገት ዕውን መሆን የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት እንደሚያስችላቸው በመታመኑ፤

enable them to identify their roles in advance and to make their contributions for the realization of the all–rounded development and progress of the region;

የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ከተሞች ማቋቋሚያ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 91/1996 የክልሉ ከተሞች ደረጃ መመዘኛና የሚደራጁበት ደንብ እንደሚወጣ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የደነገገ በመሆኑ፤

Whereas, Article 4 sub – article 2 of the revised Amhara National Regional Cities Establishment, Organization and Determination of powers and Duties proclamation No. 91/2003 stipulates that regulations would be issued setting the criteria for grades of cities and the organization thereof;

የብሔራዊ ክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 ሥር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

Now, therefore, the Council of the Amhara National Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provisions of article 58, sub-article 7 of the revised regional constitution, hereby issues this regulation:

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

## PART ONE
## GENERAL

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የከተሞች አደረጃጀትና ፈርጅ መወሰኛና ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 17/1996 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 1. Short Title

This regulation may be cited as "The Amahara National Regional State Cities Organizational Category Determination and Establishment, Council of Regional Government Regulation No. 17/2003."

### 2. የከተሞች ፈርጅና አደረጃጀት መመዘኛዎች

ከተሞች በሚከተሉት መመዘኛዎች መሠረት እንደሁኔታው ፈርጃቸው ተለይተዋል፦

ሀ. የህዝብ ብዛት
ለ. አስተዳደራዊ ማዕከልነት
ሐ. የገቢ መጠን
መ. የኗሪዎች መተዳደሪያ የሥራ መስክ
ሠ. ለወደፊት የልማት አቅጣጫ ባላቸው ስትራቴጅካዊ ጠቀሜታ።

### 2. Criteria for the Categories and Organization of Cities

Depending on the condition, categories of cities have been set on the basis of the following criteria:

a. population size
b. whether the area is a seat of administration
c. size of revenue
d. occupation of city residents
e. the strategic importance they have for future development

www.abyssinialaw.com



## 3. ከተሞችን በፈርጅ ስለመመደብ

በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ከተማ ከሚከተሉት የከተማ ፈርጆች በአንዱ ይመደባል:-

ሀ. የከተማ አስተዳደር ከተማ

ለ. የማዘጋጃ ቤት ከተማ

ሐ. ታዳጊ ከተማ

## 4. የከተማ አስተዳደር አቋም ስለማግኘት

በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም ከተማ ከዚህ በታች ከተመለከቱት መመዘኛዎች ቢያንስ አንዱን ሲያሟላ የከተማ አስተዳደር አቋም ይኖረዋል:-

ሀ. የዞን ርዕሰ ከተማ የሆነ

ለ. የጠቅላላው ኗሪ ህዝብ ብዛት 50,000 ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ወይም የመሀል ከተማውና በአቅራቢያው የሚገኙ ከተሞች ኗሪ ህዝብ 60% ሆኖ ቀሪው 40% ኗሪ ህዝብ በከተማው ወሰን ውስጥ በሚካለሉ የገጠር ቀበሌዎች የሚኖሩበት ከሆነ፣

ሐ. ለክልሉ የልማት አቅጣጫ ባለው ስትራቴጅካዊ ጠቀሜታ አኳያ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከጊዜ ወደ ጊዜ ተመሣሣይ የከተማ አስተዳደርነት አቋም የሚሰጠው ከሆነ::

## 5. የከተማ አስተዳደር ከተማ ንዑስ ፈርጆች

በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም የከተማ አስተዳደር ከተማ ከሚከተሉት ንዑስ ፈርጆች በአንደኛው ሊደራጅ ይችላል:-

ሀ. የከተማ አስተዳደር ከተማ

ለ. የአማልጋሜትድ የከተማ አስተዳደር

ሐ. የሜትሮፖሊታን የከተማ አስተዳደር

## 3. Categorization of Cities

Any city within the region shall fall into one of the following categories:

a. city administration level city

b. municipal city

c. emerging city

## 4. Acquisition of a Status of City Administrations

Any city within the region shall acquire a city administration status where it meets at least one of the criteria indicated hereunder:

a. capital city of a zone;

b. the size of the resident population is 50,000 or more or the residents of city at the center and of cities in the vicinity constitute 60% of the population while the remaining 40% of the population resides in the rural Kebeles that are located within the boundaries of the city;

c. where the Council of the Regional Government bestows upon it similar city administrative status from time to time in view of the strategic importance the city has for the development of the region.

## 5. Sub-Categories of City Administration Level City

Any city administration level city in the region may be organized under one of the following sub-categories:

a. city administration level city

b. Amalgamated City Administration

c. Metropolitan city Administration

www.abyssinialaw.com



**6. የከተማ አስተዳደር ከተማን በንዑስ ፈርጆች ለመፈረጅ ስለሚያገለግሉ መመዘኛዎች**

የከተማ አስተዳደር ከተሞች በሚከተሉት መመዘኛዎች መሠረት በየንዑሳን ፈርጆች ተለይተዋል፡-

1. የሜትሮፖሊታን የከተማ አስተዳደር መመዘኛዎች፡-
   ሀ. 50,000 እና ከዚያ በላይ የሚደርስ የመሀል ከተማ ኗሪ ህዝብ መገኘትና በአማካኝ 20 ኪሎ ሜትር ራዲየስ በሚደርስ ርቀት ያሉ ከተሞች የየራሳቸውን የአካባቢ አስተዳደር አቋም እንደያዙ በጋራ የሚተሳሰሩባቸው፣ የሚደጋገፉባቸውና የሚወስኑባቸው ጉዳዮች መኖር፣
   ለ. ይህንን የጋራ አስተዳደር የሚፈጥሩት ከተሞች አጠቃላይ የነዋሪ ሕዝብ ብዛት 100,000 እና ከዚያ በላይ ሆኖ ሲገኝ እና፣
   ሐ. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሲፈቅድ።
2. የአማልጋሜትድ የከተማ አስተዳደር መመዘኛ
   ከአንድ በላይ የሆኑና ከ10 ኪሎ ሜትር ራዲየስ ውስጥ ሆነው በመልከአምድር በኩታገጠም የሚገናኙ ከተሞችና የገጠር አካባቢዎች መገኘትና ለተመጣጣኝ ዕድገትና ለአገልግሎት አውታሮች አቅርቦት ሆነ ስርጭት የሚማከሉበትና የሚሰባሰቡበት ሁኔታ መኖር።
3. የከተማ አስተዳደር ከተማ መመዘኛ
   ከዚህ በላይ በአንቀጽ 4 ሥር የተመለከቱት መስፈርቶች የአንዱ ተሟልቶ መገኘት።

**7. የማዘጋጃ ቤት ከተማ መመዘኛዎች**

የማዘጋጃ ቤት ከተማ አቋም ለማግኘት ብቁ የሚሆን ከተማ ከዚህ በታች ከተመለከቱት መመዘኛዎች አንዱን ያሟላ መሆን ይኖርበታል፡-

**6. Criteria for the Sub-Categorization o city Administration level cities**

City Administration level cities have been sub categorized on the basis of the following criteria;

1. **Criteria for metropolitan cit Administration:**
   a. Resident population of the city at th center is 50,000 or more and citie within the average radius of 20 kms while maintaining their individual loca administration status, enjoy commo factors around which they intertwine support each other and make decisions;
   b. The total population of the cities whic institute this joint administration i 100,000 or more; and;
   c. Where the Council of the Regiona Government approves th categorization.
2. **Criteria for Amalgamated Cit Administration**
   Where condition is such that more than on cities or rural areas that are within a radius o 10 kilometers and are adjacent to each othe may be centered by and gather around th purpose of balanced growth and the suppl and distribution of service infrastructures.
3. **Criteria for city Administration leve city**
   The fulfillment of one of the criteria indicate under article 4 here of.

**7. Criteria for Municipal City**

To obtain a municipal city status a candidat urban center has to meet one of the followin criteria:

www.abyssinialaw.com



መመዘኛዎች አንዱን ያሟላ መሆን ይኖርበታል:-

ሀ. ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት ከተማ፣

ለ. 5,000 እና ከዚያ በላይ ነዋሪ ሕዝብ ያለው ማናቸውም ከተማ፣

ሐ. 3,000 እና ከዚያ በላይ ነዋሪ ሕዝብ ኖሮት የወረዳ ማዕከል የሆን ከተማ፣

መ. ለወደፊቱ የክልሉ የልማት አቅጣጫ ባለው ጠቀሜታ ለክልል መስተዳድር ምክር ቤት ጥያቄ ቀርቦ ተመሣሣይ አቋም እንዲያገኝ የሚፈቀድለት ከተማ::

## 8. የመሪ ማዘጋጃ ቤት ከተማ መመዘኛዎች

1. ማናቸውም ከተማ ከዚህ በታች ከተመለከቱት መመዘኛዎች አንዱን ወይም ሌላውን ሲያሟላ በመሪ ማዘጋጃ ቤትነት ይደራጃል:-

ሀ. የከተማው ተነፃፃሪ ጠቀሜታ ለወደፊት የልማት አቅጣጫ የሚኖረው አስተዋፅኦ፣

ለ. በወረዳው ውስጥ ከሚገኙት ከተሞች ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት ብልጫ ያለው፣

ሐ. በወረዳው ውስጥ ከሚገኙት ማዘጋጃ ቤቶች የመጨረሻዎቹ 5 ዓመታት የአማካይ ገቢው ብልጫ ያለው፣

መ. የተሻለ የከተማ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚታይበት ወይም አብዛኛው (50+1% እና ከዚያ በላይ) የከተማ ሕዝብ ከግብርና ውጪ ባለ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የተሰማራበት፣

ሠ. ቀደም ሲል ማዘጋጃ ቤት ያልተቋቋመበት ቢሆንም በአብዛኛዎቹ መመዘኛዎች የተሻለ ከተማ ሆኖ በመገኘቱ በአዲስ መልክ በማዘጋጃ ቤትነት ሲደራጅ::

2. ሆኖም በአንድ ወረዳ ውስጥ ያሉት ከተሞች የማዘጋጃ ቤት ደረጃን ለማግኘት የማይበቁ ከሆንና አስቀድሞ አንድ ማዘጋጃ ቤት ብቻ ካለ ይህ ማዘጋጃ ቤት መሪ ማዘጋጃ

a. the urban center where a municipality has been established prior to the enactment of this regulation;

b. any urban center that has a population of 5,000 or more;

c. an urban center that has a population of 3,000 or more and is a seat of the Woreda Administration;

d. where in view of its importance for future development of the region, a city for which an application presents to and would be allowed to have similar status by the Council of the Regional Government.

## 8. Criteria for Lead Municipal City

1. An urban center shall be organized as a Lead Municipal City where it meets any one of the following criteria:

a. The contribution of the comparative advantage of the urban center that make for future development.

b. The population size is much higher than the rest of the urban centers in the Woreda.

c. The average income for the last 5 years is higher than the municipalities in the Woreda

d. A better urban economic activity transpires or the majority (50 + 1% andmore) of the urban population is engaged in non-agricultural economic activity.

e. Although no municipality has been established previously, the urban center fares better by most of the criteria and is therefore established as a municipality

2. Where however, the urban centers in a Woreda fail to qualify a municipal status and there is only one municipality before, this municipality may serve as a lead

www.abyssinialaw.com



ቤት ከተማ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 9. የንዑስ ማዘጋጃ ቤት ከተማ መመዘኛ

በዚህ ደንብ አንቀጽ 7 ሥር የተመለከተውን የማዘጋጃ ቤት ከተማ መመዘኛዎች የሚያሟላና በአንቀጽ 8 ሥር ከተጠቀሰው ውጭ የሆነ ማናቸውም ከተማ በንዑስ የማዘጋጃ ቤት ከተማነት ታውቆ ይደራጃል፡፡

## 10. ስለታዳጊ ከተማ መመዘኛዎች

ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ቢያንስ አንዱን የሚያሟላ ከተማ ታዳጊ ከተማ ተብሎ ይደራጃል፡-

ሀ. ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት በክልሉ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በመደበኛ ከተማነት የታወቀና የማዘጋጃ ቤትነት መመዘኛዎችን ለማሟላት ያልበቃ፤

ለ. 2000 እና ከዚያ በላይ የከተማ ነዋሪ ሕዝብ ኖሮት አብዛኛው ነዋሪ ( 50+1% እና ከዚያ በላይ ) ከግብርና ውጪ በሆነ የኢኮኖሚ ዘርፍ ውስጥ የተሰማራ፤

ሐ. የሕዝብ ቁጥር ከግምት ውስጥ ሣይገባ ማንኛውም የወረዳ ማዕከል ከተማ ሆኖ የሚያገለግል ከተማ፡፡

## 11. ከተሞችን ስለማቋቋም

በክልሉ የሚገኙ ከተሞች ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው አባሪ እንደተመለከተው በየፈርጃቸ ተቋቁመዋል፡፡

## 12. የከተማ ፈርጆችን ስለማሻሻል

1. የከተማ ፈርጆች አመዳደብ ልዩ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር በየአምስት ዓመቱ ይከለሣል፡፡
2. የከተማ ፈርጅ አመዳደብ ማሻሻያ ጥያቄ በሚመለከተው ከተማ ሲቀርብ የክልሉ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ አስፈላጊነቱን ሲያምንበት ጥናት ካደረገ በኋላ በክልል መስተዳድር ምክር

municipality.

## 9. Criteria for Sub-Municipal City

Where any urban center that meets the criteria municipal city indicated under article 7 her and falls outside those indicated under artic shall be established as a sub-municipal city.

## 10. Criteria for Emerging Cities

An urban center that meets at least one o criteria listed here-under shall be establi as an emerging city:

a. Recognized by the Regional Burea Works and Urban Development pri the issuance of this regulation regular urban center and fails to mee criteria for municipality.

b. Having 2,000 and more city dwe where the majority of its resi (50 +1% and more) is engaged in agricultural economic sector.

c. An urban center that serves as a of the Woreda Administr irrespective of the size of its populat

## 11. Establishment of Cities

Cities found in the region are hereby establ under the respective categories indicated i annex attached hereto.

## 12. Adjustment of City Categories

1. Except under special circumstance categorization of cities shall be revi every five years.
2. Where an application for an adjustm the categorization of a city is subr by a concerned city and wher Regional Bureau of Works and

www.abyssinialaw.com



ቤቱ ውሣኔ የሚያገኝ ይሆናል::

## ክፍል ሁለት
## ስለከተሞች ወሰንና አከላለላቸው

### 13. የከተማ አስተዳደር ከተማ ወሰን

1. የከተማ አስተዳደር ከተማ ወሰን በዚህ ደንብ መሠረት ከከተማው የማዕከላዊ ስፍራ በመነሣት በዙሪያው እንደሁኔታው በ5 ኪሎ ሜትር ራዲየስ ዙሪያ ያለውን መልከዓምድራዊ ክልልና በውስጡ የሚኖሩ ሕዝቦችን ያጠቃለለ ይሆናል::
   በዚህ ወሰን የሚታቀፉት የክልሉ ከተሞች የሚከተሉት ናቸው:-
   - ሀ. የደብረብርሃን ከተማ
   - ለ. የደብረማርቆስ ከተማ
   - ሐ. የደብረታቦር ከተማ
   - መ. የወልዲያ ከተማ
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት የከተማ አስተዳደር ከተሞች ወሰን ከየከተሞቹ ማዕከላዊ ሥፍራ በመነሣት በዙሪያቸው እንደሆኔታው በ3 ኪሎ ሜትር ራዲየስ ዙሪያ ያለውን መልከዓምድራዊ ክልልና በውስጡ የሚኖሩ ሕዝቦችን ያጠቃለለ ይሆናል::
   በዚህ ወሰን የሚታቀፉት ከተሞች ከዚህ በታች የተመለከቱት ይሆናሉ:-
   - ሀ. የፍኖተ ሰላም ከተማ
   - ለ. የእንጅባራ ከተማ
   - ሐ. የሰቆጣ ከተማ
   - መ. የከሚሴ ከተማ

Development belives the necissity conducts research, and decisions shall be made thereafter by the Council of the Regional Government.

## PART TWO
## BOUNDARIES OF CITIES AND THE DELINEATION THEREOF

### 13. Boundaries of the City Administration Level City

1. Pursuant to this regulation, the boundaries of a city administration level city shall, depending on circumstances, encompass all land with in a radius of 5 kilometers from the center of the city and all people living therein. The following are the regional cities embraced by this boundary.
   - a. The city of Debre Berhan
   - b. The city of Debre Markos
   - c. The city of Debre Tabor
   - d. The city of woldia
2. Without prejudice to the provisions of sub-article 1of this article, the boundaries of the following city level cities shall, depending on the condition, encompass the surounding geographic region lying within radius of 3 kilometers from the center of the city and the people living therein.
   The following are the cities embraced by this boundary:
   - a. The city of Finote Selam
   - b. The city of Enjibara
   - c. The city of Sekota
   - d. The city of Kemisse

www.abyssinialaw.com



## 14. የሜትሮፖሊታን ከተማ አስተዳደር ከተማ ወሰን

የሜትሮፖሊታን ከተማ አስተዳደር ከተማ ወሰን ከማዕከላዊ የከተማው ስፍራ በመነሣት በአካማካይ፦

ሀ. ዙሪያውን እንደሁኔታው በ10 ኪሎ ሜትር ራዲየስ የሚገኘውን መልክአምድራዊ ክልልና በውስጡ የሚገኘውን ኗሪ ህዝብ፣

ለ. በአማካኝ 20 ኪሎ ሜትር ራዲየስ የሚገኙ የተወሰነ የአካባቢ አስተዳደር አቋም ያላቸው ከተሞችንና በውስጣቸው የሚገኘውን ኗሪ ህዝብ ያጠቃልላል:: በዚህም መሠረት የሚከተሉት ከተሞች በሜትሮፖሊታን ከተማነት ተደራጅተዋል::

1. በባህርዳር ከተማ ማዕከልነት፦
   - የጢስ አባይ፣
   - የመሸንቲና
   - የዘጌ ከተሞች
2. በጎንደር ከተማ ማዕከልነት- የጠዳ ከተማ
3. በደሴ ከተማ ማዕከልነት - የኮምቦልቻ ከተማ

## 14. The Boundaries of a Metropolitan Administration Level City

Measured at an average, starting fron center of the city, the bounderie metropolitan administration level city encompass:

a. depending on the conditions, surrounding gepgraphic region within radius of 10 kilometers ar population living therein.

b. cities with a defined local administ status found with in an average rad 20 kilometers and the population therein. Accordingly, the foll cities are hereby establishec metropolitan cities

1. The city of Bahr Dar as the cen
   - Tis Abay
   - Meshenti and
   - Zege Cities.
2. Gonder as the center - Teda c
3. Dessie as the center - Koml city

## 15. የማዘጋጃ ቤት ከተሞች ወሰን

የመሪና የንዑስ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች ወሰን ከየከተሞቹ ማዕከላዊ ቦታ በመነሣት በዙሪያቸው እንደከተማው ዕድገት ደረጃ ከ1 እስከ 2 ኪሎ ሜትር ራዲየስ ያለውን መልከዓምድራዊ ክልልና በውስጡ የሚኖሩ ሕዝቦችን ያጠቃለለ ይሆናል::

## 15. Boundaries of Municipal Cities

Boundaries of Lead and Sub-municipal shall, depending on development level o city, include the surrounding geographic with in a radius of 1 to 2 kilometers frc center of the city and population living tł

## 16. የታዳጊ ከተሞች ወሰን

የታዳጊ ከተሞች ወሰን ከከተማው ማዕከላዊ ቦታ በመነሣት በዙሪያው እንደከተማው ዕድገት ሁኔታ ከ0.5 እስከ 1 ኪሎ ሜትር ራዲየስ ያለውን መልከዓምድራዊ ክልልና በውስጡ የሚኖሩ ሕዝቦችን ያጠቃለለ ይሆናል::

## 16. Boundaries of Emerging Cities

The boundaries of emerging cities depending on the development level o city, include the surrounding geographic with in a radius of 0.5 to 1 kilometers a population living therein.

www.abyssinialaw.com



## 17. ስለ ከተሞች ወሰን አካላይ ኮሚቴ

1. አግባብነት ባላቸው የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት የከተማ አስተዳደር ከተሞችን ወሰን የሚከልል ኮሚቴ በዞን አስተዳደር ምክር ቤት ይሰየማል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም የባህር ዳር ከተማንና በዚሁ ከተማ አማካኝነት የሚማከሉትን የሜትሮፖሊታን ከተሞች ወሰን አካላይ ኮሚቴ የሚሠየመው በክልል መስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የማዘጋጃ ቤትና የታዳጊ ከተሞች ወሰን አካላይ ኮሚቴ የሚቋቋመው በሚመለከተው ወረዳ አስተዳደር ም/ቤት ይሆናል፡፡

## 17. City Boundary Delineating Committee

1. In accordance with the relevant provision of this regulation, a committee to delineate the boundaries of city administration level cities shall be designated by the zonal administrative council.
2. Notwithstanding sub article 1 hereof, the Boundary Delineating Committee for Bahr Dar city and the metropolitan cities that are centered by this city shall be designated by the Council of Regional Government.
3. Without prejudice to the provisions of sub-articles 1 and 2 hereof, the Boundary Delineating Committee for municipal and emerging cities shall be designated by the concerned Woreda Administrative Council.

## 18. ስለ ኮሚቴው አሰራርና ኃላፊነት

1. የከተሞች ወሰን አካላይ ኮሚቴ የማዘጋጃ ቤትና የታዳጊ ከተሞች ወሰን ለመከለል የሚጠቀምበትን ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ የክልሉ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ይህን ደንብ መሠረት አድርጐ ያወጣል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም የከተማ አስተዳደር ከተሞች ወሰን በዝርዝር የሚሠራው የክልሉ ንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ውጤታማ የመሬት አጠቃቀምን፣ አስተዳደራዊ ምቹነትንና የመሳሰሉትን ታሳቢዎች ግምት ውስጥ አስገብቶ በሚያወጣው መመሪያና የዚህ ደንብ ክፍልና አካል በሆነው አባሪ 2 በተመለከተው አኳኋን ይሆናል፡፡

## 18. Working Procedures and Responsibilities of the Committee

1. The Regional Bureau of Works and Urban Development shall, pursuant to this regulation, issue the detailed implementation directives that the Boundary Delineating Committee uses to delineate the boundaries of municipal and emerging cities.
2. Notwithstanding sub- Article 1 hereof, the detailed delineation of the boundaries of city administration level cities shall be worked out on the basis of directives to be issued by the Trade, Industry and Urban Development Bureau taking into account such factors as the effective utilization of land and administrative conveniences and in line with annex 2 which is an integral part and parcel of this regulation.

www.abyssinialaw.com



## 19. ዝርዝር ወሰኑን ስለማፅደቅ

1. የወሰን አካላይ ኮሚቴው ለከተማ አስተዳደር የሠራው ዝርዝር ወሰን ለዞን አስተዳደር ምክር ቤት ቀርቦ ይፀድቃል::
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ደንጋጌ ቢኖርም የባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ወሰን በክልሉ መስተዳደር ም/ቤት ወይም እሱ በሚወክለው አግባብ ይፀድቃል::
3. የማዘጋጃ ቤትና ታዳጊ ከተሞችን ዝርዝር ወሰን የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ያፀድቃል::

## 20. የከተማ ወሰንን ስለማሻሻል

የአንድ ከተማ ወሰን እላይ በተዘረዘሩት አግባቦች ከተከለለ በኋላ እንደከተማው የዕድገት ሁኔታ ማሻሻል ሲያስፈልግ የሚመለከተው ከተማ አስተዳደር ጥያቄውን ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል::

# ክፍል ሦስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 21. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

አሁን ያለው የምርጫ ዘመን ተጠናቆ አዲስ ምርጫ እስከሚካሄድ እና በዚህ ደንብ መሠረት የሜትሮፖሊታን ከተማ ምክር ቤት እስከሚደራጅ ድረስ:-

1. የባህር ዳር፣ የጐንደርና የደሴ ከተማ አስተዳደሮች በየበኩላቸው በሜትሮፖሊታን አቋም የሚያማክሏቸውን ከተሞች የኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳይ በኃላፊነት ተረክበው እየመሩ ይቆያሉ::

## 19. Approval of Detailed Boundary L

1. Detailed boundaries prepared b Boundary Delineating Committee sl presented to and approved by the Administrative Council.
2. Notwithstanding sub article 1 here( boundaries of the Bahr Dar administration shall be approved t Council of the Regional Governm( another body that the council designate.
3. Detailed boundaries of municipal emerging cities shall be approved t woreda administrative council.

## 20. Adjustment of City Boundaries

Where, after the boundaries of a city have delineated in the manner specified abov ajustment thereof becoms necessary depe on the progress of the city, the concerne( administration may submit its request t( Concil of the Regional Government approval.

# PART THREE
# MISCELLANEOU!
# PROVISIONS

## 21. Transitory Provisions

Until the current electoral term expires, a election held and a metropolitan city co formed in accordance herewith:

1. The Bahr Dar, Gonder and Dessie administrations shall respectively delivery of and direct the economic, s( and political affairs of the cities they ce as metropolitan entities.

www.abyssinialaw.com



2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ደንጋጌ ቢኖርም የኮምቦልቻ ከተማ ለሽግግር ጊዜው የራሱን የከተማ አስተዳደር አቋም እንደያዘ ይቆያል::

22. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ይህን ደንብ ለማስፈፀም የሚረዱ መመሪያዎችን የክልሉ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ሊያወጣ ይችላል::

23. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልል መስተዳድር ምክር ቤቱ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባህር ዳር

ሰኔ 28 ቀን 1996 ዓ.ም.

ዮሴፍ ረታ

የአማራ ብሔራዊ ክልል

ርዕሰ መስተዳድር

2. Notwithstanding the provision of sub-article 1 hereof, the city of Kombolcha shall continue to manage its own city administration during the transition period.

### 22. Power to Issue Directives

The Regional Bureau of Works and Urban Development may issue directives necessary for the implementation of this regulation.

### 23. Effective Date

This Regulation shall come into force as of the day of its approval by the Council of the Regional Government.

**Done at Bahr Dar**

This 5th day of July, 2004

**YOSEF RETA**

**Head of the Government of the Amhara National Regional State**

www.abyssinialaw.com



## የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
## የከተሞች አመዳደብ ሠንጠረዥ 1

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የከተማ አስተዳደር ከተሞች፣ የሜትሮፖሊታን ከ
አስተዳደር ከተሞች፣ የመሪ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች ፣ንዑስ ማዘጋጃ ቤትና ታዳጊ ከተሞች ዝርዝ

### የከተማ አስተዳደር ከተሞች

ሀ. ሜትሮፖሊታን የከተማ አስተዳደር

1. ባህርዳር
2. ጎንደር
3. ደሴ

ለ. የከተማ አስተዳደር ከተሞች

1. ደብረ ብርሃን 2. ደብረ ማርቆስ 3. ወልዲያ 4. ደብረ ታቦር
5. ከሚሴ 6. ሰቆጣ 7. እንጅባራ 8. ፍኖተ ሰላም

ሐ. የማዘጋጃ ቤትና የታዳጊ ከተሞች ምደባ ዝርዝር

| ዞን | ወረዳ | መሪ ማዘጋጃ ቤት | ንዑስ ማዘጋጃ ቤት | ታዳጊ ከተማ |
|---|---|---|---|---|
| 1. ሰሜን ጎንደር | • አዲአርቃይ | • አዲአርቃይ | - | • ዛሪማ |
| | • በየዳ | -- | -- | • ድልይብዛ |
| | • ጃንአሞራ | -- | -- | • መካነ ብርሃን |
| | • ደባርቅ | • ደባርቅ | -- | -- |
| | • ዳባት | • ዳባት | -- | • ወቅን |
| | • ታች አርማጭሆ | • ሳንጃ | • አብደራፊ | - |
| | • ጠገዴ | - | -- | ቅራቅር |
| | • ወገራ | • አምባጊዮርጊስ | • ገደብየ | -- |
| | • ደንቢያ | • ቆላድባ | • ጫሂት | • ጎርጎራ<br>• አይንባ |
| | • ጭልጋ | • አይከል | • ነጋዴ ባህር | • ሰረባ |
| | • መተማ | • ሽሂዲ | • መተማ ዮሐንስ<br>• ኮኪት | • ሽንፋ<br>• ቁመት |
| | • ቋራ | -- | -- | • ቴወድሮስ ከተማ<br>• ገላጉ |
| | • አለፋ ጣቁሣ | • ደልጊ | • ሻሁራ | • ጎመንጌ<br>• ደንገል በር |
| | • ምዕራብ በለሣ | • አርባያ | -- | • አርባ ፀጋር |
| | • ጎንደር ዙሪያ | • ማክሰኝት | • እንፍራዝ<br>• ጠዳ | • ደጎማ |
| | • ላይ አርማጭሆ | • ትክል ድንጋይ | -- | -- |
| | • ምስራቅ በለሣ | • ዙይ ሐሙሲት | • ጉህላ | -- |
| ድምር | 17 | 13 | 10 | 16 |

www.abyssinialaw.com



| ዞን | ወረዳ | መሪ ማዘጋጃ ቤት | ንዑስ ማዘጋጃ ቤት | ታዳጊ ከተማ |
|---|---|---|---|---|
| 2. ደቡብ ጎንደር | እብናት | እብናት | -- | -- |
| | ለቦ ከምከም | አዲስ ዘመን | -- | • ይፋግ<br>• አምቦሜዳ |
| | ፎገራ | ወረታ | -- | • አመድበር |
| | ፋርጣ | ክምር ድንጋይ | -- | • ጋሣይ |
| | ላይ ጋይንት | ነፋስ መውጫ | -- | • ጎብጎብ |
| | ታች ጋይንት | አርብ ገበያ | -- | -- |
| | ስማዳ | ወግዳ | -- | -- |
| | እስቴ | መካነ ኢየሱስ | -- | • ጃራገዶ |
| | ደራ | ሀሙሲት | አምበሣሜ | • አርብ ገበያ |
| ድምር | 9 | 9 | 1 | 7 |
| 3. ሰሜን ወሎ | ቡግና | ላሊበላ | -- | -- |
| | ቆቦ | ቆቦ | ሮቢት | • ጎብዩ |
| | ግዳን | -- | -- | • ደብረፀሐይ<br>• ሙጃ |
| | መቄት | ፍላቂት-ገረገራ | -- | -- |
| | ዋድላ | -- | | • ኮን |
| | ዳውንት ደላንታ | ውገል ጤና | -- | -- |
| | ሀብሩ | መርሣ | ውርጌሣ | -- |
| | ጉባላፍቶ | -- | ሃራ | • ሣንቃ<br>• ዶሮ ግብር |
| ድምር | 8 | 5 | 3 | 6 |
| 4. ደቡብ ወሎ | መቅደላ | ማሻ | -- | -- |
| | ተንታ | አጅባር | ተንታ | -- |
| | አምባሰል | ውጫሌ | -- | -- |
| | ተሁለደሬ | ሀይቅ | -- | • ባሶሚሌ<br>• ሱሉላ |
| | ወረባቦ | ቢስቲማ | -- | • ቦከክሣ |
| | አልብኮ | -- | -- | • ደጋጋ |
| | ቃሉ | ሀርቡ | -- | • ገርባ<br>• ደጋን |
| | ለጋንቦ | አቀስታ | -- | • አንባሙበር |
| | ሣይንት | አጅባር | -- | -- |
| | ደብረሲና | መካነ ሰላም | -- | -- |
| | ከለላ | ከለላ | -- | • ሉጋማ |
| | ጃማ | ደጉል | -- | -- |
| | ወረኢሉ | ወረኢሉ | -- | • ካቤ<br>• ወይን አምባ |
| | ወግዲ | ወግዲ | -- | • ማህደረ ሰላም |
| | ደሴ ዙሪያ | -- | -- | ጢጣ |
| | ኩታ በር | ኩታ በር | -- | -- |
| ድምር | 16 | 14 | 1 | 12 |

www.abyssinialaw.com



| ዞን | ወረዳ | መሪ ማዘጋጃ ቤት | ንዑስ ማዘጋጃ ቤት | ታዳጊ ከተማ |
|---|---|---|---|---|
| 5. ሰሜን ሸዋ | ሜዳና ወራም | መራኛ | -- | • ዳማ |
| | መረሃቤቴ | አለም ከተማ | -- | • ፌጢራ |
| | አንጣሮና ዋዩ | ደነባ | -- | • ለሚ |
| | ሞረትና ጅሩ | እነዋሪ | -- | • ጅሁር |
| | ጊራቀያ | መሀል ሜዳ | -- | -- |
| | ግሸ | -- | -- | • ራቤል |
| | አንጾኪያና ገምዛ | ማጀቴ | • መኮይ | -- |
| | ኤፍታና ግድም | አጣዬ | • ካራቆሬ | • ጀውሃ |
| | ላሉማማ ምድር | ሞላሌ | -- | -- |
| | ጣርማ በር | ደብረ ሲና | -- | • መዘዞ |
| | ቀወት | ሸዋ ሮቢት | -- | -- |
| | አንጎለልና ጠራ | ጫጫ | -- | -- |
| | አሣግርት | -- | -- | • ጊናገር |
| | ሙጃና ወደራ | -- | -- | • ሰላ ድንጋይ |
| | አንከበር | -- | ጉረቤላ | • አልዩአምባ |
| | በረኸት | -- | -- | • መተህ ብላ |
| | ምንጃርና ሸንኮራ | አረርቲ | -- | • ባልጪ |
| | ሀገረ ማሪያም ከሰም | -- | -- | • ሾላ ገበያ |
| | ባሶና ወረና | -- | -- | • ጉዶ በረት |
| ድምር | 19 | 12 | 3 | 14 |
| 6.ምዕራብ ጎጃም | አቸፈር | ዱርቤቴ | • ቁንዝላ | • ይስማላ |
| | ይልማና ዴንሣ | አዴት | -- | -- |
| | ሜጫ | መርዓዊ | ወተት አባይ | -- |
| | ሰከላ | -- | -- | • ግሽ አባይ |
| | ቋሪት | -- | ገበዘ ማሪያም | -- |
| | ደጋ ዳሞት | -- | -- | • ፈረስ ቤት |
| | ደምበጫ | ደምበጫ | -- | -- |
| | ጃቢ ጠህናን | ጅጋ | -- | • ማንኩሣ |
| | ቡሬ | ቡሬ | -- | -- |
| | ወንበርማ | ሸንዲ | -- | -- |
| | ባህርዳር ዙሪያ | ዘጌ | ጢስ አባይ | • መሸንቲ |
| ድምር | 11 | 8 | 4 | 5 |
| 7.ምስራቅ ጎጃም | ቢቡኝ | | -- | • ደጎፅዩን |
| | ሁለት እጁ እነሴ | ሞጣ | -- | • ሰዴ |
| | ጎንቻ ሲሶ እነሴ | ጉንደ ወይን | -- | |
| | እነሴ ሣር ምድር | መርጦ ለማሪያም | -- | |
| | እናርጅ እናውጋ | ደብረ ወርቅ | -- | • ፈለገ ብርሃን |
| | እነማይ | ብቸና | -- | • የትመን |
| | ደባይ ጥላት ግን | ቀይ | -- | |
| | ማቻከል | አማኑኤል | -- | |
| | ደብረ ኤልያስ | ኤልያስ | -- | |
| | ባሶ ሊበን | የጁቤ | -- | • ኮርከ |
| | ጎዛምን | ሮብ ገበያ | -- | • የቦቅላ |
| | አዋበል | ሉማሜ | -- | • ወጀል<br>• አምበር |
| | ደጀን | ደጀን | -- | |
| | ሸበል በረንታ | | -- | • የዱሃ |
| ድምር | 14 | 12 | -- | 9 |

www.abyssinialaw.com



| ዞን | ወረዳ | መሪ ማዘጋጃ ቤት | ንዑስ ማዘጋጃ ቤት | ታዳጊ ከተማ |
|---|---|---|---|---|
| 8. አዊ | ዳንግላ | ዳንግላ | -- | • ደቅ |
| | ባንጃ ሸኩዳድ | ቲሊሊ | -- | • ከሳ |
| | አንከሻ ጓጉሣ | አገው ግምጃ ቤት | -- | • አዘና |
| | ጓንጓ | ቻግኒ | መንታ ውሃ | • ቅላጅ |
| | ፋግታ ለኮማ | አዲስ ቅዳም | -- | -- |
| ድምር | 5 | 5 | 1 | 4 |
| 9. አሮሚያ | ደዋ ጨፋ | -- | -- | • ቦራ<br>• ወለዲ |
| | ባቲ | ባቲ | -- | -- |
| | አርጡማ ፉርሲ | ጨፋ ሮቢት | -- | -- |
| | ጅሬና ጥሙጋ | ስንበቴ | | |
| ድምር | 4 | 3 | -- | 1 |
| 10.ዋግ ኽምራ | ዝቋላ | -- | -- | ሲያለዋ/ፅፅቃ/ |
| | ስቆጣ | ስቆጣ | -- | -- |
| | ዳህና | አምደ ወርቅ | -- | -- |
| ድምር | 3 | 2 | -- | 1 |
| ጠ.ድምር | 106 | 83 | 23 | 75 |

www.abyssinialaw.com



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የከተማ አስተዳደር ከተሞች ወሰን አመልካች ሠንጠረ

ዕዝል /አባሪ/2

| ተ.ቁ | የከተማው ስም | የሚያካልላቸው /የሚያቅፋቸው የገጠር ቀበሌዎች | ም ር መ ራ |
|---|---|---|---|
| 1 | ባህር ዳር ከተማ | ድሽት፣ አባራጅ፣ ወረብ ቋራዕዮን፣ ዘንዘልማ፣ ወራሚት | |
| 2 | ዘጌ | ወንጃጣ | |
| 3 | ጭስዓባይ | ማጂ ደ/ንግሥት፣ ይጋንዲ ፣ወልቀያ ዳስራ፣ ወፍ አርግፍና ዘመቻ አቦ | |
| 4 | መሸንቲ | መሸንቲ አቸዳ | |
| 5 | ደሴ ከተማ | ግራዶ፣ ሰዮጠቢላ፣ በሩ ሜጠሮ ቆርኬ፣ ቀለምደረባ፣ ደሬ፣ ቂሊና ጢጣ | |
| 6 | ኮምቦልቻ | ከዲዳ፣ መተናይ ጋሌሳ፣ ታይአምባ ጃራጀሮ፣ አባኮልባ፣ ስዬጃንጥራር፣ አንቻሮአርፎ | |
| 7 | ጎንደር | ሎዛ ማርያም፣ አዘዞ ተ/ሐይማኖት፣ ማሪያም ደብር፣ ፈንጠር፣ ክልል እየሱስ፣ ሰሆርና ደፈጫ፣ ድብ አቦ፣ ብላጅግ አባእንጦኒዬስ፣ አንቺው፣ ሳቢያ ላይና | |
| 8 | ጠዳ | ላይጠዳ ፣ ታችጠዳ | |
| 9 | ደብረማርቆስ | እንራታ፣ ቀቢ፣ ጭምቦርድ፣ ወንቃ የቦ፣ የወቤ እነችፎ | |
| 10 | ደብረ ታቦር | ዊብላ ሰላምኮ፣ ሂሩይና አባረጋይ፣ ደብረ ታቦር እየሱስ፣ ፀጉር አዲኮ | |
| 11 | ፍኖተሠላም | ባከል፣ አባተር፣ ሸንበቆማ፣ አርባይቱ እንሰሳ | |
| 12 | እንጅባራ | ቻባና ጊሳ፣ ባሳ እንጓና፣ ጂባ ባህንክ፣ ቢዳጀጉለ፣ ባታ አምቢ፣ አካይታ ጋሽና፣ ይፍራታ | |
| 13 | ሰቆጣ | አንድነት፣ ወቀሬ | |
| 14 | ከሚሴ | ከሚሴ አካባቢ፣ ጉዳገሪ | |
| 15 | ወልድያ | ጉላመቻሬ፣ መሀልመቻሬ፣ ጀነቶ በር፣ ጉባራጀ፣ ገብርኤል አደንጉር | |
| 16 | ደብረብርሃን | ጠባሲ፣ ካራፌኖ አታክልት፣ ዘንጀራ ወለጨና ጠደአምባ፣ ጢቢ ገነቴና ወልደተንሳይ | |

ጠጠ

www.abyssinialaw.com



**Amhara National Regional State City categorization Table 1**

The Amhara National Regional State list of City Administration Level Cities, Metropolitan City Administration Cities, Lead Municipal Cities, Sub-Municipal and Emerging Cities.

City Administration Level Cities

a- Metropolitan City Administration

1. Bahr Dar
2. Gonder
3. Dessie

b- City Administration Level Cities

1. Debre Berhan
2. Debre Marqos
3. Weldia
4. Debre Tabor
5. kemise
6. Seqota
7. Engibara
8. Fenote Selam

c- List of Categories of Municipal and Emerging Cities

| Zone | Wereda | Lead municipality | Sub municipality | Emerging city |
|---|---|---|---|---|
| 1. Semien Gonder | Adiarqay | Adiarqay | - | • Zarima |
| | Beyeda | - | - | • Delyebeza |
| | Janamora | - | - | • Mekane Berhan |
| | Debarq | Debarq | - | - |
| | Dabat | Dabat | - | • Weqen |
| | Tache Armacheho | Sanja | - Abderafe | |
| | Tegede | - | - | • Qeraqer |
| | Wegera | Ambagiyorgis | Gedebye | - |
| | Denbiya | Qoladeba | Chuahit | • Gorgora<br>• Aynba |

www.abyssinialaw.com



| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | Chelga | Aykel | Negadie Bahir | • Sereba |
| | Metema | Shehidi | Metema Yohannes<br>Kokit | • Shenfa<br>• Tumet |
| | Quara | - | - | • Tewodros Ketema<br>• Gelagu |
| | Alefa Taqusa | Delgi | Shahura | • Gomengie<br>• Dengel Ber |
| | Merab Belesa | Arbaya | | • Arba Tseguar |
| | Gonder Zuriya | Makesegnit | • Enfraz<br>• Teda | • Degoma |
| | Lay Armacheho | Tekel Dengay | - | - |
| | Mesraq Belesa | Zuy Hamusit | Guhela | - |
| **Total** | **17** | **13** | **10** | **16** |

| Zone | Wereda | Lead municipality | Sub municipality | Emerging city |
|---|---|---|---|---|
| **2.Debub Gonder** | Ebenat | Ebenat | - | - |
| | Libo Kemkem | Addis Zmen | - | • Yefag<br>• Ambomeda |
| | Fogera | Wereta | - | • Amedber |
| | Farta | Kemer Dengay | - | • Gasay |
| | Lay Gayent | Nefas Mewcha | - | • Gobgob |
| | Tache Gayent | Arb Gebeya | - | - |
| | Semada | Wegda | - | - |
| | Este | Mekane Eyesus | - | • Jaragedo |
| | Dera | Hamusit | Ambesamy | • Arbgebeya |
| **Total** | **9** | **9** | **1** | **7** |
| | Bugna | Lalibela | - | - |
| | Qobo | Qobo | Robit | • Gobiyu |

www.abyssinialaw.com



| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3.Semien Wello | Gedan | - | - | • DebreTsehaye<br>• Muja |
| | Meqet | Felaqit Geragera | - | - |
| | Wadla | - | - | • Kon |
| | Dawent Delanta | Wegel Tena | - | - |
| | Habru | Mersa | Wurgsa | - |
| | Gobalafto | - | Hara | • Sanqa<br>• Doro Geber |
| **Total** | **8** | **5** | **3** | **6** |

| Zone | Wereda | Lead municipality | Sub municipality | Emerging city |
|---|---|---|---|---|
| 4.Debub Wello | Meqdela | Masha | - | - |
| | Tenta | Ajbar | Tenta | - |
| | Ambasel | Wuchale | - | - |
| | Tehuledre | Hayeq | - | • Basomily<br>• Sulula |
| | Werebabo | Bistima | - | • Bokeksa |
| | Albeko | - | - | • Degaga |
| | Qalu | Harbu | - | • Gerba<br>• Degan |
| | Leganbo | Aqesta | - | • Anbachober |
| | Sayent | Ajbar | - | - |
| | Debresina | Mekanselam | - | - |
| | Kelela | Kelela | - | • Lugama |
| | Jamma | Degol | - | - |
| | Wereilu | Wereilu | - | • Kabe<br>• Weyn Amba |
| | Wegdi | Wegdi | - | • Mahdereselam |
| | Dessiezuriya | - | - | ▪ Tita |
| | Kuta Ber | Kuta Ber | - | - |
| Total | **16** | **14** | **1** | **12** |

www.abyssinialaw.com



| Zone | Wereda | Lead municipality | Sub municipality | Emerging city |
|---|---|---|---|---|
| 5.Semien Shoa | Medana Weram | Meragna | - | • Dama |
| | Merhabete | Alem Ketema | - | • Fetira |
| | Enesarona Wayu | Deneba | - | • Lemi |
| | Moretena Jeru | Enewari | - | • Jehur |
| | Geraqeya | Mehal Meda | - | - |
| | Geshe | - | - | • Rabel |
| | Antsokiana Gemza | Majete | Mekoy | - |
| | Eftana Gedem | Ataye | Karaqori | • Jaweha |
| | Lalumama Meder | Molale | - | - |
| | Tarma Ber | Debre Sina | - | • Mezezo |
| | Qewet | Shoa Robit | - | - |
| | Angolelana Tera | Chacha | - | - |
| | Asagert | - | - | • Ginager |
| | Mujana Wedera | - | - | • Sella Dengay |
| | Ankober | - | - Gorebela | • Alyuamba |
| | Berehet | - | - | • Meteha Bela |
| | Menjarena Shenkora | Arerti | - | • Balchi |
| | Hagere Mareyam Kesem | - | - | • Shola Gebeya |
| | Basona Werena | - | - | • Gudo Beret |
| Total | 19 | 12 | 3 | 14 |

www.abyssinialaw.com



| Zone | Wereda | Lead municipality | Sub municipality | Emerging city |
|---|---|---|---|---|
| 6.Mierab Gojam | Achefer | Durbete | Qunzela | • Yesmala |
| | Yelmana Densa | Adet | - | - |
| | Mecha | Mereawi | Wetet Abay | - |
| | Sekela | - | - | • Gesh Abay |
| | Quarit | - | Gebeze Mariyam | - |
| | DegaDamote | - | - | • Feres bet |
| | Dembecha | Dembecha | - | - |
| | Jabi Tehnan | Jega | - | • Mankusa |
| | Bure | Bure | | - |
| | Wenbrema | Shendi | - | - |
| | Baherdar Zuriya | Zege | Tis Abay | • Meshenti |
| Total | 11 | 8 | 4 | 5 |
| 7.Mesraq Gojam | Bibugne | - | - | • Degotsion |
| | Hulet Eju Ennesie | Mota | - | • Sede |
| | Goncha Siso Ennese | Gunde Weyn | - | - |
| | Enesi Sar Meder | Merto Lemariam | - | - |
| | Enarj Enawga | Debre Worq | - | • Felege Berhan |
| | Enemay | Bichena | - | • Yetmen |
| | Debay Telat Gin | Quy | - | - |
| | Machakel | Amanuel | - | - |
| | Debre Elias | Elias | - | - |
| | Baso Liben | Yejube | - | • Kork |
| | Gozamen | Rob Gebeya | - | • Yebokila |
| | Awabel | Lumame | - | • Wojel<br>• Amber |
| | Dejen | Dejen | - | |
| | Shebel Berenta | - | - | • Yeduha |
| Total | 14 | 12 | - | 9 |

www.abyssinialaw.com



| Zone | Wereda | Lead municipality | Sub municipality | Emerging city |
|---|---|---|---|---|
| 8. Awi | Dangla | Dangla | - | • Deq |
| | Banja Shekudad | Tilili | - | • Kessa |
| | Ankesha Guagusa | Agew Gemja bet | - | • Azenna |
| | Guangua | Chagni | Menta Weha | • Qelaj |
| | Fageta Lekoma | Addis Qdam | - | - |
| **Totol** | 5 | 5 | 1 | 4 |
| 9.Oromiya | Dewa Cheffa | - | - | • Bora<br>• Woledi |
| | Bati | Bati | - | - |
| | Artuma Fursi | Cheffa Robit | - | - |
| | Jerena Tmuga | Senbete | - | - |
| **Total** | 4 | 3 | - | 1 |
| 10. Wag Hemra | Zequala | - | - | • Siyalewa /Tseaeqa/ |
| | Seqota | Seqota | - | - |
| | Dahena | Amde Werq | - | - |
| **Total** | 3 | 2 | - | 1 |
| **Grand Total** | 106 | 83 | 23 | 75 |

www.abyssinialaw.com



## able Showing the Boundaries of the Amhara National Regional State City Administration Level Cities (Annex 2)

| er.No. | Name of the City | Rural Kebeles it Encompasses | Remarks |
|---|---|---|---|
| 1. | Baheredar City | Deshet, Abaraje, Wereb Quaratsion, Zenzelma, Weramit | |
| 2. | Zege | Wenjata | |
| 3. | Tisabay | Maji D/Negest, Yegandi, Welqaya Dasra, Wof Argef ena Zemecha Abbo | |
| 4. | Meshenti | Meshenti Acheda | |
| 5. | Dessie City | Grado, Seyotebila, Beru Metero Qorke, Kelem Dereba, Dere, Kili Ena Tita | |
| 6. | Kombolcha | Kedida, Metenai Galessa, Tayamba Jarajero, Abakolba, Seyejantrar, Ancharoerafo | |
| 7. | Gonder | Loza Mariam, Azezo T/Haymanot, Mariam Deber, Fenter, Kilil Eyesus, sihorena Defecha, Dib Ambo, Belajeg Abaentoniyos, Anchiw, Sabiya Layena . | |
| 8. | Tedda | Laytedda, Tachtedda | |
| 9. | Debre Markos | Enerata, Kebi, Chimbord, Wenka Yebo, Yewobe Enechefo, | |
| 10 | Debre Tabor | Wibla Selamko, Hiruyna Abaregay, Debre Tabor Eyesus, Tsegur Adico, | |
| 11. | Finoteselam | Bakel, Abater, Shenbekoma, Arbayetu Ensesa | |
| 12. | Enjibara | Chabenagia, Basa Enguana, Jiba Bahunk, Bidajegole, Bata Ambie, Akayta, Gashena Yifrata | |
| 13. | Sekota | Andanet, Woqere, | |
| 14. | Kemise | Kemise Akababi, Godageri | |
| 15. | Weldeya | Golamechare,Mehalmechare, Jeneto Ber, Gubaraje, Gebreal Adengur | |
| 16. | Debre Berhan | Tebassi, Karafino Atakilt, Zenjera Welechena, Tedeamba, Tibi Genetena Weldetenesay, | |